

# " እንኩሃንም ከናንተ ጓሮ በቀልኩ!"

የጐንቻው!

"እንኩሃንም ከናንተ ጓሮ በቀልኩ!"

'ካድዋም አድዮ' ሁኘ ገዘፍኩ፤

'እህል ሰቡን' እያቀጨጭኩ፤

ዘር መርጨ ባጋዚ እያጨድኩ፤

'የነፃነት ወለድ እዳ እያስከፈልኩ፤

ትውልድ አራጣ ባላንጣ እያስገበርኩ፤

'እንኩሃን መቶ ዓመት 'ሺ' የታደልኩ፤

**"እንኩሃንም ከናንተ ጓሮ በቀልኩ!"።**

"እንኩሃን ደስ አላችሁ! 'ደስ አለኝ!'፤

ከለም ምድር 'ከወርቅ ዘር' ስገኝ፤

ከምርጡ ዘር ስብጥር ማዳበሪያ ብናኝ፤

ጐርፍ ያመጣኝ ወፍ የዘራኝ፤

ያባቴ ፍግ ፋንድያ ያበቀለኝ፤

የበኩር ልጅ 'አለሌው' የመረጠኝ፤

'ታላቁ መሪ' 'ጉዲፈቻ' ያሳደገኝ፤

'አፌም ጥርሴም ትግራዊ ቅኝ'፤

'ዕዳ ጠቅላይ' ሚኒስቴር ነኝ፤

**"እንኩሃን ደሰ አላችሁ!"፤ 'ደሰ አለኝ!'።**

ቀልጨ እንደ ሰም ከትብቴ አፈር፤

'ነብይ' ያዩት 'ራዕያቸው' ሲተገበር፤

በትንሣዔዬ አበቅቴ የቃል ምድር፤

እንዳዋልድ 'ሐዲስ አገር'፤

በአጽሙ ካሳ ሕዝቡ እንዲጦር፤

እንድትከፍል ኢትዮጵያ የደም ግብር፤

**ሕዝቧ ሚሊዮን የነፍስ ዋጋ ነፃ ይቁጠር።**

**የጐንቻው!** 15/02/15
yegonchaw@yahoo.co.uk